ፊንላንድ

# የእርስዎ የመቀበያ (የመስተንግዶ) መብቶችና ግዴታዎች



**የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚመለከቱዎት ከሆነ፣ ይህ መረጃ የተዘጋጀው ለእርስዎ ነው፦**

- **እርስዎ አዋቂ (ከ18 ዓመት በላይ) ነዎት**
- **ለዓለም አቀፍ ጥበቃ (ጥገኝነት ተብሎም ይጠራል) በፊንላንድ ማመልከት እንደሚፈልጉ በ ለባለሥልጣናት አሳውቀዋል፣ አሁን ደግሞ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ነዎት።**

**እርስዎ በዚህ ሀገር ውስጥ ደኅንነትዎ የተጠበቀ ነው።**

AMHARIC

## መቀበያ (መስተንግዶ) ማለት ምን ማለት ነው?

መቀበያ (መስተንግዶ) ማለት ባለሥልጣናት የእርስዎን የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ እስከሚመረምሩበት ጊዜ ድረስ እንደ አመልካችነት የሚያገኙት ድጋፍ ነው። በዚህ መግለጫ ውስጥ የተብራሩትን የመቀበያ መብቶችና ግዴታዎች ያካትታል።

በፊንላንድ የመቀበያ ጉዳዮችን የሚያስተዳድረው ባለሥልጣን የኢሚግሬሽን ቢሮ ነው። ማመልከቻዎን የሚመረምር እና የሚያስተናግድ ባለሥልጣንም የኢሚግሬሽን ቢሮ ነው።



የኢሚግሬሽን ቢሮ ወይም የመቀበያ ማዕከ ሰራተኞቹ  በዚህ መግለጫ ውስጥ ያለውን መረጃ መቀበልዎን እንዲያረጋግጡና እንዲፈርሙ ይጠይቁዎታል። ማመልከቻዎን ከማስመዝገብዎ በፊት ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ

አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ **ተርጓሚ** በሚረዱት ቋንቋ ከሠራተኞቹ ጋር እንዲነጋገሩ ይረዳዎታል። ተርጓሚው የሚናገሩትን ለሌላ ማንኛውም ሰው አያካፍልም።

**ስለ ጥገኝነት አሠራርና ስለሚከተሏቸው ሕጎች በተለያዩ ብሮሸሮች ውስጥ መረጃ ያገኛሉ።**

እንዲሁም ከሌሎች ድርጅቶች በነፃ መረጃና እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ። በዚህ ብሮሸር መጨረሻ ላይ የድርጅቶችን ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ።

**አሁን የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር በሆነችው በፊንላንድ ውስጥ ነዎት።**
**የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገራት የሚከተሉት ናቸው፡-**

- 27 የአውሮፓ ኅብረት (EU) አባል ሀገራት፡- ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሳይፕረስ፣ ቼኪያ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ ጣሊያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ የአየርላንድ ሪፐብሊክ፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፔን፣ ስዊድን እና
- 4 ሌሎች ሀገራት፡- አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድ።

## ትኩረት!

ለጥገኝነት ስለማመልከት እና ወደ ሌሎች የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገራት ስለመጓዝ የተቀመጡ ሕጎች አሉ።

- ባለሥልጣናት ሌላ ካልነገሩዎት በስተቀር፣ **ለጥገኝነት ማመልከትና ማመልከቻዎን ለመጀመሪያ ጊዜ በደረሱበት የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ማስመዝገብ አለብዎ።**
- **የእርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አንድ የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ብቻ ነው።** በፊንላንድ ውስጥ ያሉት ባለሥልጣናት ለጥገኝነት ማመልከቻዎ የትኛው የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ኃላፊ የሚወስድ እንደሆነ ለመወሰን አንድን አሠራር ይከተላሉ።
- **በፊንላንድ ውስጥ መቆየት አለብዎ። ያለ ባለሥልጣናት ፈቃድ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር መጓዝ አይችሉም።** ከለቀቁ፣ አሉታዊ ውጤቶች ይኖራሉ። በፊንላንድውስጥ ያለው የጥገኝነት አሠራርዎ ሊቆም ይችላል። በሌላኛው ሀገር የመንቀሳቀስ ነፃነትዎ ሊገደብ ይችላል፣ እንዲሁም አንዳንድ የመቀበያ አገልግሎቶች ይሰረዛሉ።

# ምን ያገኛሉ?

መቀበያ ገንዘብ (vastaanottoraha) ካስፈለገዎት፣ ከሚኖሩበት የመቀበያ ማዕከል ማመልከት አለብዎት። በማመልከቻዎ ውስጥ ስለ ገቢዎችዎ እና ስለ ያሉዎት ንብረቶች/ገንዘቦች ማብራሪያ መስጠት አለብዎት።”



- መጠለያ



- የግል ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች



- ምግብ



- ልብስ





- የዕለት ወጪ የሚሆን ገንዘብ

*[አባል ሀገር ይህ እንዴት እንደሚሰጥ በመወሰን በጥሬ ገንዘብ ወይም በካርድ የሚያሳይ አርማ መምረጥ ይችላል፤ የማይሠራውን አርማ ያስወግዱ።]*

የመቀበያ ማዕከሉ ሰራተኞች የግል ሁኔታዎን እና የገንዘብ ሁኔታዎን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ጥያቄዎችን ይጠይቁዎታል።

ድጋፍና አገልግሎቶችን የሚያገኙት ባለሥልጣናት በወሰኑበት ቦታ ብቻ ይሆናል።


## የጤና እንክብካቤ መብት

ባለሥልጣናት **የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ** ማግኘትዎን ያረጋግጣሉ።



እርስዎ ከሐኪም ወይም ከነርስ ጋር የሕክምና ምርመራ ሊያደርጉ ይችላሉ]። ጤንነትዎን በመመርመር ይረዱዎታል።

## ለሠራተኞቹ ያሳውቁ፣ የሚከተለው ከሆነ፦



- ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ እና ያለወላጆችዎ፣ ብቻዎን ወይም ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ጋር ከመጡ
- ታመው ወይም ተጎድተው ከሆነ
- እርጉዝ ከሆኑ ወይም ሊሆኑ ከቻለ
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የቤተሰብ አባላት ካሉዎት
- አካል ጉዳት ካለብዎ
- በየጊዜው ሀዘን ጭንቀት ከተሰማዎት፣ መተኛት ካልቻሉ ወይም አሉታዊ ሐሳቦች ካሉዎት
- ጥቃት ደርሶብዎ ከሆነ
- ደኅንነትዎ የተጠበቀ እንዳልሆነ ከተሰማዎት ወይም የአንድን ሰው ፍርሃት ካለብዎ
- ሌላ ድጋፍ የሚፈልግ ሁኔታ ውስጥ ነዎት

**እርስዎን መርዳት እንዲችሉ ሠራተኞቹን ማመን እና በግልጽ ማነጋገር ይችላሉ።** ሁሉም መረጃ ሚስጥራዊ ሆኖ ይቆያል፣ ይህም ማለት ያለእርስዎ ስምምነት ለሌሎች አይጋራም ማለት ነው።

ብቸኛው ልዩነት የእርስዎ ወይም የሌላ ሰው ሕይወት አደጋ ላይ ሲወድቅ ነው።

## የሕፃናት የትምህርት መብት



ሁሉም ሕፃናት፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከ18 ዓመት በታች የሆኑየትምህርት መብት አላቸው።

## የሥራ እና የኮርሶችን የመከታተል መብት







በሁኔታዎ ላይ በመመስረት፣ ከፊንላንድ በተወሰኑ ሁኔታዎች ስር የመሥራት መብት ሊኖርዎ ይችላል ። ሠራተኞቹ በምን ዓይነት ሁኔታዎች ስር የመሥራት መብት እንዳለዎት ያሳውቁዎታል።

እንዲሁም ሊከታተሉዋቸው ስለሚችሉ ኮርሶች ይነግሩዎታል።

## የት ይቆያሉ?



[*ክፍል/አፓርትመንት ለሚከራዩ አመልካቾች አበል ለሚሰጡ አባል ሀገራት አማራጭ ነው*] ባለሥልጣናት የት እንደሚቆዩ ይነግሩዎታል እንዲሁም ሁኔታዎቹን ያስረዳሉ።

የእርስዎ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ በሚመረመርበት ጊዜ የሚቆዩበት ቦታ በብዙ ሁኔታዎች ላይ ይመሰረታል።

## ባለሥልጣናት በተወሰነ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ውስጥ እንዲቆዩ ሊወስኑ ይችላሉ

### ትኩረት!

**ባለሥልጣናት በተወሰነ ቦታ** (ለምሳሌ በተወሰነ የመቀበያ ማዕከል ውስጥ) መቆየት እንዳለብዎ ሊወስኑ ይችላሉ።

ከተወሰኑ ገደቦች ጋር ከዛ የተወሰነ ቦታ መውጣት ይችላሉ። በዛ የተወሰነ ቦታ መገኘትዎ  ሊረጋገጥ ይችላል።



### የትም ይሁኑ የት፣ የሚከተሉት መብት አለዎት፦



- **ደኅንነትዎን ይጠብቁ፦** ሠራተኞችን ጨምሮ ማንም ሰው እርስዎን ማስፈራራት፣ መስደብ ወይም ጉዳት ማድረስ አይፈቀድለትም



- **ከባልዎ፣ ከሚስትዎ፣ ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ ልጆችዎና እህትማማቾችዎ ጋር ወይም የዕለት ተዕለት እንክብካቤ ከሚያስፈልገው ጎልማሳ ዘመድዎ ጋር መቆየት**
- **ከዘመዶችዎ ጋር መቆየት፣** እርስዎ የዕለት ተዕለት እንክብካቤ ከሚያስፈልግዎ ጎልማሳ ከሆኑ



- **ቤተሰብዎ የት እንዳሉ** የማያውቁ ከሆነ፣ **ከእነሱ ጋር ለመነጋገር እና ለመፈለግ እርዳታ ያግኙ።**

# አመልካች ሊታሰር የሚችልባቸው ሁኔታዎች

እስር ማለት በነፃነት መውጣት በማይችሉበት በተወሰነ ስፍራ መቀመጥ ማለት ነው። ባለሥልጣናት እርስዎን ለማሰር ትክክለኛ ምክንያት ሊኖራቸው ይገባል። በእርስዎ ጉዳይ ሌላ አማራጭ እንደሌለ እርግጠኛ መሆን አለባቸው። ፖሊስ እና የድንበር ጥበቃ ባለሥልጣን ከመወሰናቸው በፊት የእርስዎን የግል ሁኔታ ይመለከታሉ።



የመታሰር ምክንያቶች ለምሳሌ፡-

- የጥገኝነት ማመልከቻዎ አስፈላጊ ገጽታዎች (ለምሳሌ የእርስዎ ማንነት) ያለእስር ማረጋገጥ ካልተቻለ
- በተወሰነ በታ የመቆየት ግዴታዎን ካላከበሩ፣ እና እንደገና የመሸሽ እና ባለሥልጣናት እርስዎን ማግኘት የማይችሉበት ስጋት ካለ
- የጥገኝነት ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ወደሚኖርበት የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር የመዛወር ውሳኔ ከተቀበሉ እና ከመዛወርዎ በፊት የመሸሽ ስጋት ካለ
- የደኅንነት ስጋት ከፈጠሩ።

ከታሰሩ፣ ውሳኔውን መቃወም (ይግባኝ ማለት) ይችላሉ። ነፃ የሕግ ድጋፍና ውክልና መጠየቅ ይችላሉ።



## በዚህ ደረጃ የመቀበያ (የመስተንግዶ) ግዴታዎችዎ ምንድን ናቸው?

**ከዚህ በታች መከተል ያለብዎት አንዳንድ ግዴታዎች ቀርበዋል።**



- የዚህችን ሀገር ሕጎች መከተል።
- በፊንላንድ ውስጥ መቆየት እና ያለባለሥልጣናት ፈቃድ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር አለመጓዝ።
- ባለሥልጣናት እንዲቆዩበት ካሉበት ቦታ ያለፈቃድ አለመውጣት።
- በሚቆዩበት ቦታ ደንቦችን ማክበር።
- የግንኙነት አድራሻዎን ለባለሥልጣናት ማሳወቅ።

## ግዴታዎችዎን ካልተከተሉ ምን ይከሰታል?

ባለሥልጣናት ሁኔታዎን ይገመግማሉ እና የሚወስዷቸውን ማንኛቸውም እርምጃዎች ያሳውቁዎታል።

**ለምሳሌ፣ ባለሥልጣናት እንዲቆዩበት ከወሰኑበት** ቦታ ያለፈቃድ ከወጡ ወይም በሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ለጥገኝነት አመልክተው ከዚያ ከለቀቁ፣ የሚያገኙት ድጋፍ ሊቀንስ ይችላል።

ጠበኛ ከሆኑ፣ ሌሎችን ካስፈራሩ ወይም የሚቆዩበትን ቦታ ሕጎች በተደጋጋሚ ወይም በከባድ ሁኔታ ከጣሱ፣ **የሚሰጥዎትን ድጋፍ ሊያጡ ይችላሉ።**





## ያለ ባለሥልጣናት ፈቃድ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ቢጓዙ ምን ይከሰታል?




በፊንላንድ ውስጥ፦

- የጥገኝነት አሰራርዎ ሊቆም ይችላል።

**ያለፈቃድ በሄዱበት የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ውስጥ፦**

- ባለሥልጣናቱ ያለፈቃድ ወደ ለቀቁት ሀገር ሊመልሱዎት ሊወስኑ ይችላሉ።

ሀገርዎን መልሰው የመላክ ውሳኔን ባለሥልጣናቱ ካሳወቁበት ጊዜ ጀምሮ የተወሰኑ መብቶችን የማግኘት መብት አይኖርዎትም ለምሳሌ፦

- **በርካታ የድጋፍ ዓይነቶችን አያገኙም**
- **እንዲሠሩ ወይም ኮርሶችን እንዲከታተሉ አይፈቀድልዎትም።**

## የባለሥልጣናትን ውሳኔ መቃወም (ይግባኝ ማለት) ይችላሉ፣ እንዲሁም የሕግ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ

ባለሥልጣናት እንደ አመልካችነት መብትዎን ለመገደብ ከወሰኑ እና ይህ ፍትሐዊ አይደለም ብለው ካመኑ፣ **ውሳኔውን መቃወም (ይግባኝ ማለት) ይችላሉ።**

በሁኔታዎ ላይ በመመስረት፣ ነፃ የሕግ ድጋፍና ውክልና ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ ማለት የሕግ አማካሪ ወይም ጠበቃ ይረዱዎታል ማለት ነው።

ስለሚገኝ ነፃ የሕግ ድጋፍና ውክልናን ጨምሮ ለበለጠ መረጃ ባለሥልጣናትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ወይም ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር. (UNHCR)ን መጠየቅ ይችላሉ።

ባለሥልጣናት የሚሰጥዎትን የመቀበያ ድጋፍ ለመቀነስ ወይም ለመሰረዝ ከወሰኑ፣ አሁንም ቢሆን የተወሰኑ መብቶች ይኖሩዎታል። አሁንም የሚያገኙት የድጋፍ ዓይነት በግል ሁኔታቸውና በፍላጎታቸው ላይ ይመሰረታል።

# የእውቂያ ዝርዝሮች

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወይም በሚቆዩበት ጊዜ ድጋፍ ካስፈለገዎት፣ በሚከተሉት ውስጥ ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋር መነጋገር ይችላሉ፡-

[**አግባብነት ያለው ባለሥልጣን**
የእርሶ የመቀበያ ማዕከል

**ሌላ አግባብነት ያለው ባለሥልጣን**
የኢሚግሬሽን ቢሮ (Maahanmuuttovirasto)
ፖ.ሳ.ቁ. 10, FI-00086 Maahanmuuttovirasto, ኢሜይል: migri@migri.fi

**የሕግ ምክር፣ የሕግ እርዳታ እና የሕግ ውክልና**
የሕግ እርዳታ በመንግስት የሕግ እርዳታ ቢሮዎች፣ በሕግ ቢሮዎች እና በጠበቆች ይሰጣል።
ስለ የሕግ ተወካዮች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ የሚኖሩበትን መቀበያ ማዕከል ይጠይቁ።
ድህረ ገጽ: oikeuspalveluvirasto.fi/yhteystiedot

**UNHCR (የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን)** የጥገኝነት ጠያቂዎችን እና ስደተኞችን መብቶችና ጥቅሞች ይጠብቃል።
ቅርብ የUNHCR ክልላዊ ቢሮ: United Nations High Commissioner for Refugees (UNHCR)
አድራሻ: Wenner-Gren Center, Sveavägen 166, 11346 Stockholm, Sweden
ኢሜይል: swest@unhcr.org

ሌሎች የመገናኛ አድራሻዎች
የእኩልነት ኦምቡድስማን (Yhdenvertaisuusvaltuutettu),ፖ.ሳ.ቁ. 24, FI-00023 Valtioneuvosto, ኢሜይል: yvv@oikeus.fi , ድህረ ገጽ: www.syrjinta.fi

ድንገተኛ የሕክምና ችግር ካለብዎት ወይም በአደጋ ውስጥ ከሆኑ፣ በነጻ ወደ 112 የአስቸኳይ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል ይችላሉ።

Maahanmuuttovirasto
Migrationsverket
Finnish Immigration Service

RAJAVARTIOLAITOS
GRÄNSBEVAKNINGSVÄSENDET
FINNISH BORDER GUARD

POLIISI
POLICE OF FINLAND

euaa
EUROPEAN UNION
AGENCY FOR ASYLUM

Co-funded by
the European Union

ይህ ብሮሸር ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። የአውሮፓ ኅብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) የዚህን ጽሑፍ ዋና ክፍል አቅርቧል፣ እና የዚህ መግለጫ ቅጂ ማውጣትና ማሻሻያ ማድረግ የተፈቀደው ለአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ብቻ ነው። የEUAA በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ወይም በሌላ ማንኛውም ኃላፊነት ባለው ሶስተኛ ወገን በዚህ ብሮሸር ውስጥ የተካተተው መረጃ ትክክለኛነት፣ ይዘት፣ ሙሉነት፣ ሕጋዊነት ወይም አስተማማኝነት ላይ ምንም ዓይነት ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነትን አይቀበልም። በዚህ ብሮሸር ላይ ካለ መረጃ ሊገኝ ስለሚችል ጥቅም EUAA ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025

Publications Office
of the European Union

ISBN 000-00-00-00000-0
doi:00.0000/0000000
AA-00-00-000-AM-C